ETHIOPIAN ASSOCIATION IN THE GREATER TORONTO AREA & SURROUNDING REGIONS
የኢትዮጵያውያን ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው
1950 Danforth Avenue, Toronto, Ontario , M4C 1J4
Tel: (416) 694 1522 E-mail: info@ethioassociation.org www.ethioassociation.org

የካቲት 1 ቀን 2015

## ከኢትዮጵያ ማህበር የተሰጠ መግለጫ

የኢትዮጵያ ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው ከዚህ በፊት በሀገራችን ኢትዮጵያም ሆነ በሌላ አገር በኢትዮጵያውያን ላይ ግድያ ሲፈጸም፣ ግፍና ስቃይ ሲደርስ፣ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሲፈጸሙ ድርጊቱን ሲያወግዝና የተቃውሞ ድምጹን ሲያሰማ መቆየቱ ይታወሳል።

ላለፉት ጥቂት ዓመታት በኢትዮጵያውያን ላይ በዘራቸው እየተለዩ ሲጨፈጨፉ፣ እጅግ ዘግናኝ ግድያዎች በየክልሉ ሲካሄዱ፣ በዓለም ወስጥ በከፍተኛ ደረጃ የውስጥ ሕዝብ መፈናቀል ሲደርስ፣ የጦር ወንጀል በሚያሰኝ ደረጃ ወንጀል ሲፈጸም፣ የሰብዓዊ መብቶች ሲጣሱና ሰቃይ መከራ በኢትዮጵያውያን ላይ ሲደርሱ ማየትና መስማት እጅግ ልብ የሚያደማና የሚያሳዝን ነው።

የኢትዮጵያ ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው እነዚህ ሁሉ ድርጊቶች በማውገዝ ተቃውሞውን በሰላማዊ ሰልፎች በመግለጽና የተቃውሞ መግለጫ በማውጣት ለኢትዮጵያ መንግስት፣ ለተባበሩት መንግስታትና ለአፍሪካ ህበርት ሲያሰማ እንደነበረው ሁሉ፤ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ሀገራችንን ጨርሶ ሊያጠፋት የሚችል በዘመናችን አይተን ሰምተን የማናውቀው በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያ ላይ የመከፋፈል ድርጊት፣ አማኞች ላይ ግድያ፣ ግፍና መከራ እየደረሰ መሆኑን ማህበሩን እጅግ አሳስቦታል። ኢትዮጵያውያን በሀገራችንና በመላው ዓለም በሀዘንና በጭንቀት ላይ ሲሆኑ እንደዚሁም በቶሮንቶና አካባቢው ያሉትም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ይገኛሉ።

በተለይም የኢትዮጵያ መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ላይ ቀጥተኛ የሆነ ተሳትፎ በማድረግ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ላይ እጁን በማስገባት ንጹሀን የተዋህዶ አማኞች ላይ ግድያ፣ ማቁሰልና ድብደባ ፈጽሟል፣ የሃይማኖት አባቶችን ገድሏል፣ አስሯል፣ አንገላቷል፣ አዋርዷል። ቤተክርስቲያንን በመድፈርና ስብሮ በመግባት ለህገወጥ ቡድን ስጥቷል። ይህ በዘመናችን ተፈጽሞ የማይታወቅ አደጋና ድርጊት መላውን ኢትዮያውያንን የሀዘን ማቅ እንዲለብሱ ማድረጉን በእጅጉ ያወግዛል። ይኮንናል።

የኢትዮጵያ ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው ይህ አገር የማፍረስ፣ ቤተክርስቲያንን የማጥፋትና በኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞች ላይ የሚፈጸመው ግድያ መከራና ግፍ እንዲቆም ጥሪውን ለዓለም ሕብተረሰብ ያሰማል፣ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ላይ የኢትዮጵያ መንግሥት እጁን እንዲያነሳ ይጠይቃል። በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እንዲከበሩ ድምጹን ያሰማል።

በሀገራችን ሰላም እንዲሰፍን፣ ግድያ መፈናቀልና ማዋከብ እንዲቆም፣ ሕዝብ በነጻነት እንዲንቀሳቀስ ድጋፍ ለማድረግ የሚቻለውን ሁሉ ማህበራችን ያደርጋል። በኢትዮጵያ የተለያዩ እምነቶች ተከባብረው በሰላም ለብዙ ዓመታት የኖሩት የሃይማኖት አባቶች ለእምነቱ ተከታዮች ፍቅርና ሰላምን እያስተማሩ እየሰበኩ ሁሉም በእምነቱ በሰላም ሲኖር መንግሥት ጣልቃ እየገባ አባቶችን በመከፋፈልና በደል በማድረስ ሰላም የኖረችውን ሀገራችንን ሰላም መንሳቱ አሳሳቢና ተጠያቂ የሚያደርግ በመሆኑ፤ የኢትዮጵያ መንግሥትም በአስቸኳይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶን ቤተክርስቲያን በይፋ ይቅርታ እንዲጠይቅና የእርምት እርምጃ እንዲወስድ፣ ሕግም እንዲያከበርና እንዲያስከብር በአጽንኦት ያሳስባል።

የኢትዮጵያ ማህበር በስሞኑ በሻሸመኔ እንዲሁም በሎችም ቦታዎች ግድያ ሕይወታቸውን ላጡ ሰማዕታት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ አባቶች፣ ካህናትና ምዕመናን ጥልቅ ሀዘኑን እየገለጸ፣ እግዚአብሄር ነፍሳቸውን በገነት እንዲያኖረው እንዲሁም ለቤተሰቦቻቸው ሁሉ መጽናናትን እንዲሰጥ ይመኛል።

የኢትዮጵያ ማህበር በቶሮንቶና አካባቢው